የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፭
አዲስ አበባ—ጥቅምት ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፭

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

9th Year No. 5
ADDIS ABABA–31st October, 2002

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፪፻፺፫/፲፱፻፺፭ ዓ.ም
ለጎሬ–ጋምቤላ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ከዓረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት የተገኘው ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ...................................... ገጽ ፩ሺ፱፻፴፭

## CONTENTS

Proclamation No. 293/2002
Arab Bank for Economic Development in Africa Loan Agreement for Financing the Gore-Gambella Road Project Ratification Proclamation ........................................ Page 1935

### አዋጅ ቁጥር ፪፻፺፫/፲፱፻፺፭

### በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዓረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለጎሬ–ጋምቤላ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል መጠኑ ፲፫ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር /አሥራ ሦስት ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር/ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዓረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት መካከል እ.ኤ.አ. ሜይ ፴፩ ቀን ፪ሺ፪ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፣

መሠረታዊ የኢኮኖሚ ዓለም አቀፍ ውሎች ተፈፃሚ ከመሆ ናቸው በፊት መፅደቅ ስላለባቸው፣

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥቅምት ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፣

በሕገ–መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ /፩/ እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለጎሬ–ጋምቤላ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ከአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት የተገኘው ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፪፻፺፫/፲፱፻፺፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### *PROCLAMATION NO. 293/2002*

### *A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE ARAB BANK FOR ECONOMIC DEVELOPMENT IN AFRICA*

WHEREAS, a Loan Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Arab Bank for Economic Development in Africa stipulating that the Arab Bank for Economic Development in Africa provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan amount of USD. 13,000,000 (thirteen million United States Dollars) for financing the Gore-Gambella Road Project was signed in Addis Ababa on the 31st day of May, 2002;

WHEREAS, basic economic International agreements have to be ratified prior to entry into force;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said loan agreement at its session held on the 31st day of October, 2002;

NOW, THEREFORE, in accordance with Sub-Articles (1) and (12) of Article 55 of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Arab Bank for Economic Development in Africa Loan Agreement for Financing the Gore-Gambella Road Project Ratification Proclamation No. 293/2002."

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፪· <u>ትርጓሜ</u>

በዚህ አዋጅ ውስጥ "የብድር ስምምነት" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት መካከል እ·ኤ·አ· ሜይ ፴፩ ቀን ፪ሺ፪ በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ነው።

፫· <u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ ሥልጣን</u>

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፲፫ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር /አሥራ ሦስት ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር/ በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

፬· <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከጥቅምት ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ·ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ጥቅምት ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ·ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት



2. *Definition*

In this Proclamation "Loan Agreement" means the Loan Agreement signed in Addis Ababa, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Arab Bank for Economic Development in Africa on the 31st day of May, 2002.

3. *Power of the Minister of Finance & Economic Development*

The Minister of Finance & Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan amount of USD. 13,000,000 (thirteen million United State Dollars) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 31st day of October, 2002.

Done at Addis Ababa this 31st day of October, 2002.

GIRMA WOLDE GIORGIS

PRESIDENT OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE